THE EDUCATION STATE

# በደንብ በምታውቀው ቋንቋ ልጅዎን ማነጋገር

ልጆች የወላጆችን ወይም የአሳዳጊዎችን ቋንቋ ለመናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ለልጅዎ የመጀመሪያውና በጣም ጠቃሚው አስተማሪ እርስዎ ነዎት። ይህ ለእነሱ ማንነት ወይም ከየት እንደመጡ መለያ ስሜት መግለጫ ብቻ ሳይሆን፤ በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት እንዲያመጡም ይረዳቸዋል።

የራሳቸውን የመጀመሪያ ቋንቋ ከተማሩ በኋላ እንግሊዝኛ ለመማር ጊዜ ሊወስድ ይችላል፤ ነገር ግን ልጅዎ በቤት ውስጥ እንግሊዝኛ ባይናገር የሚቀርበትጥቅም አይኖርም።

## በሚገባ በሚያውቁት የአገርዎ ቋንቋ ከልጅዎ ጋር መነጋገር፣ ማንበብና መጻፍ።

በተቻለ መጠን በርስዎ አገር ቋንቋ ማነጋገር፣ ማንበብና መጻፍ አለብዎት፤ እንዲሁም ከዚህ በታች ባሉት የተለያዩ ሁኔታዎች መጠቀም:

- መዘመር፣ ማነጋገርና የተለያዩ የቁጥር ጨዋታዎችን መጫወትና በራስዎ ቋንቋ ለልጅዎ ማንባብ
- ከቤተሰብ ጋር ሲወጡና ክብረ በዓል ሲያከብሩ በራስዎ ቋንቋ መነጋገር
- ምንም እንኳን ልጅዎ በእንግሊዝኛ መልስ ቢሰጥዎም በራስዎ ቋንቋ ልጅዎን ማነጋገር ነው። ህጻናት በቋንቋዎች መካከል ያለን ልዩነት ሊሰሙ ይችላሉ፤ እንዲሁም
- በኋላም በራስዎ ቋንቋ መመሪያ በመስጠት የልጅዎንየቤት ሥራ መርዳት አለብዎ፤ ምክንያቱም በማንኛውም ያገኙት ችሎታ በትምህርትቤት ውስጥ ሊጠቅም ስለሚችል ነው። ለምሳሌ በራስዎ ቋንቋ ለልጅዎ እንዴት ማባዛት እንደሚችል  ካስተማሩት በተመሳሳይ በእንግሊዝኛ እንዴት መደረግ እንዳለበት በቀጥታ ይረዳዋል።

## የራስዎን ቋንቋ መጠበቅ የልጅዎን የወደፊት የወደፊት እድል ማሻሻል

ከልጅዎ ጋር በአገርዎ ቋንቋ አብሮ በመነጋገር፣ በማንበብና በመጻፍ  የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ እንዲሆን ይረዱታል፤ ይህም ብዙ ጥቅም አለው። የሁለት ቋንቋ እና የመድብለ-ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ህጻናት አንድ ቋንቋ ከሚናገሩ ህጻናት ፈጣን እድገት ያሳያሉ።

## የምርምር ጥናት እንደሚያሳየው: በልጅነት እድሜ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋዎችን መማር፤

**ለአእምሮ መዳበር ይረዳል;** ከአንድ ቋንቋ በላይ መናገር የህጻናትን አእምሮ ያዳብራል። እንዲሁም በበለጠ የፈጠራ አስተሳሰብ እንዲኖራቸውና ለችግሮች በቀላሉ መፍትሄ ማግኘት እንዲችሉ  ይረዳል።

**የእንግሊዝኛ መጻፍና ማንበብ ችሎታ እንዲጨምር ያደርጋል;** ከአገራቸው ቋንቋ ጋር አብሮ እንግሊዝኛ መማሩ የህጻናትን ማንበብና መጻፍ ችሎታ ለማዳበር ይረዳል; ብሎም ቋንቋ እንዴት እንደሚሰራ እና ለህጻናት የተሻሉ አንባቢዎች፣ አድማጮችና ግንኙነት ፈጣሪዎች እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

**የማስታወስ፣ የማስተዋል ትኩረትና የቁጥር ትምህርት ችሎታን ያዳብራል፤** ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋዎችን መናገሩ የህጻናትን አእምሮ "ጅማት" በማጠናከር ያላቸውን የማስታወስና የማስተዋል ችሎታ እንዲሻሻል ያደርጋል።

**በትምህርት ቤት ያለን አጠቃላይ የሥራ አፈጻጸም ያሻሽላል;** በሁለቱም ማለት በራሳቸው እናበ እንግሊዝኛ ቋንቋ ጠንካራ የሆኑ ህጻናት በደረጃ መለያ ፈተናዎች ላይ አንድ ቋንቋ ከሚናገሩት ህጻናት የተሻለ ውጤት፤በተለይም በሂሳብ፣ በማንበብና በቃላት ማወቅ የተሻለ ደረጃ ሊኖራቸው ይችላል።

**የህጻናትን ማንነት ስሜት ማጠናከር; በአገራቸው ቋንቋ የተማሩ ህጻናት ከቤተሰባቸው፤** ከማህበረሰባቸው ጋራ ዘላቂ የሆነ ጠንካራ ግንኙነት እንዲቀጥል ቀላል ያደርገዋል። ለወደፊት ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ልጅዎ በበለጠ መቀጠር እንደሚችልና ወደ ውጭ አገር በመጓዝ ለመስራት የበለጠ እድል ይኖረዋል። የቪክቶሪያ መንግሥት የቋንቋ ትምህርት እንዲጀመር በማድረጉ ልጅዎ ሌላ ቋንቋ በትምህርት ቤት ውስጥ መማርን ይጀምራል።

**ይሁን እንጂ በአገርዎ ቋንቋ ልጅዎ እንዲናገር፣ እንዲያነብ እና እንዲጽፍ ማድረጉ በጣም ወሳኝ ነው። ልጅዎ በሁለቱም ቋንቋዎች ብቃት እንዲኖረው በትክክለኛ መስመር ላይ በማስቀመጥ እንዲሁም በዚህ ሳቢያ የሚመጡት የዓለም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ዝግጁ ያደርገዋል።**



VICTORIA State Government | Education and Training